# የኀጢአት ይቅርታን ስለማግኘትና የእግዚአብሔርን ሰላም ተቀብሎ ስለመኖር የተሰጠ ማረጋገጫ

በዊልያም ጄ ፓቶን

# መግቢያ

ውድ አንባቢዬ፤

ይህቺን ትንሽ መጽሐፍ ሳቀርብልህ ዐላማዬ ያደረግሁት፣ በእግዚአብሔር ችሮታ ክርስቶስን የግል አዳኝህ አድርገህ እንድትቀበል ወይም ክርስቶስን ተቀብለህ ከሆነም የዘላለም ሕይወት እንዳለህ እርግጠኛ እንድትሆን ነው።

አንብበህ ጥቅም እንድታገኝ ስላምሻ መጽሐፏን እንዴት አድርገህ እንደምታነብባት እስቲ የሚከተለውን ጥቂት ምክር ልለግስህ።

1. ሌሎች ሰዎች በተለያየ ነገር ሳያዋክቡህ ከጌታህ ጋር ለብቻህ ጊዜ ወስደህ አንብብ።

2. በዝግታ አንብብ። እንደዚህች አይነት አነስተኛ መጽሐፍ ስታነብብ በችኮላ ማንበቡ ጥቅም የለውም።

3. ይህችን መጽሐፍ እግዚአብሔር አንተን ወደ ክርስቶስ የሚመራበት መሣሪያ አድርጎ እንዲጠቀምባት በጸሎት አንብባት።

4. ለሌሎች ሰዎች ሳይሆን ለራስህ ብለህ አንብብ። በሕይወትህም ተግባራዊ አድርገው።

ንባብህን ከመጨረስህ በፊትም፣ ያመንሁትን እርሱን ስለማውቅ አላፍርበትም፤ የሰጠሁትንም ዐደራ እስከዚያች ቀን ድረስ መጠበቅ እንደሚችል ተረድቻለሁ። (2ጢሞቴዎስ 1÷12) ለማለት እንድትችል እግዚአብሔር ይርዳህ።

ዊልያም ጄ ፓቶን ይህች ትንሽ መጽሐፍ የተዘጋጀችው ዎፓርደን ኤንድ አሹራንስ በሚል ርእስ በኖርዘርናን አየርላንድ ድሮማራ ኮዳውን ነዋሪ በሆኑት በዊልያም ጄ ፓቶን ከተጻፈው ዝነኛ መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳቡ ተወስዶ ነው።

**ትርጉም**

የኢትዮጵያ ጉባኤ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን
የመ.ሣ.ቁ. 55110
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ስልክ 22 64 93 22 64 92 **E-mail: gubae@mail.telecom.net.et**

# ክርስቲያኖች ደስተኛ የሆኑበት ምክንያት ምንድነው?

## በዊልያም ጄ ፓቶን

ክርስቲያኖች የኀጢአት ይቅርታን ድነትን የተቀበሉ ናቸው። አንድ ሰው አብዝቶ በእግዚአብሔር ላይ ኀጢአት እንደሠራ ሲረዳ፣ በዚህም ሳቢያ ወደ ሞትና ወደ ገሃነም መጣል ሲገባው፣ ክርስቶስ እንደወደደው እና የኀጢአቱን ቅጣት ሁሉ በመሸከም፣ ኀጢአቱን ሁሉ እንዳስተሰረየለትና እንዲረሳ እንዳደረገለት ሲገባው አይደሰትምን? አንድ መርከበኛስ በባሕር ላይ ሲጓዝ ከመጣበት ከባድ የባሕር ሞገድ ሲያመልጥ ደስ አይሰኝምን?

አንባቢዬ ሆይ! ኀጢአትህ ይቅር እንደተባለልህ ብታውቅ እጅግ ደስ አትሰኝ ይሆንን? ይህን ያህል አሁን ስለሞት፣ ስለፍርድ ወይም ስለ ገሃነም አታስብ ይሆናል። የእግዚአብሔር መንፈስም እነዚህን ነገሮች ወደ ሐሳብህ ቢያመጣቸው ከአእምሮህ ልታስወጣቸው ትሞክራለህ። ይሁን እንጂ ይህን ድንቅ ደስታ ለመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

*መተላለፉ ይቅር የተባለለት፣*

*ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣*

*እንዴት ብሩክ ነው!* (መዝሙር 32፥1)።

እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ይወዳል፤ እነርሱም እንዲሁ ይወዱታል። የቅርብ ወዳጅ የሆነው በየቀኑና በየሰዓቱ አብሮ የሚሆነው፣ መሪና እረኛ የሚሆነው፣ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ የሚያቀርበው ኢየሱስ እንዳለው ክርስቲያን ሲያውቅ ምንኛ ደስ ይለው! ስለዚህ ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጽፎአል፤ እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁን ባታዩትም በእርሱ ታምናላችሁ፤ መግለጽ በማይቻልና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ብሎአችኋል (1ጴጥሮስ 1፥8)።

ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያደርጋሉ፤ ይኸውም እነርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራሉ፣ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ይነጋገራል ማለት ነው። ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍቶ፦ ጌታ ሆይ፤ ተናገር ባሪያህም ይሰማል። ማለት መቻሉ ምንኛ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው! አንዳንድ ጊዜ

በጉባኤ መካከል ሆኖ በሰማያት ያለውን አባታችንን ማወደስና ከፍ ከፍ ማድረግ ወይም የጌታ እራት የምንለውን የልጁን ማእድ በታላቅ ደስታ በኅብረት መካፈል እንዴት ያለ መንፈሳዊ መቀጣጠልን የሚያመጣ ጉዳይ ነው!

ክርስቲያኖች ኀጢአትን በማሸነፋቸው፣ እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘታቸውና ለሌሎች ሰዎች መልካም ነገርን በማድረጋቸው ደስ ይሰኛሉ፡፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ትልቅ ሽልማትን እንደሚያስገኝ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (መዝሙር 19÷11)፡፡ ክርስቲያን አዳኙን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስደሰት እነዚህን ነገሮች ቢያደርግ ደስታው የበለጠ ይጨምራል፡፡

## ቀኑን ሙሉ የእግዚብሔርን ሥራ ሲሠሩ መዋል ምንኛ ጣፋጭ ነው!

እግዚአብሔር አንድን ክርስቲያን ተጠቅሞ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ ሲመራና ኃጢአተኛው ከተሳሳተ መንገዱ ተመልሶ ነፍሱ ከሞት ስትድን፤ ክርስቲያን ክፉ የሥጋ መሻቱን በመፈጸም ከሚያገኘው ጊዜያዊ ደስታ ጋር የማይወዳደር ታላቅ ሐሴት በሕይወቱ ይኖራል፡፡ ታዋቂው ማክቼኒ እንዳለው፡- ለእግዚአብሔር ቀኑን ሙሉ ሲሠሩ ውለው ማምሻውን የተሞላ ፊቱን እያዩ ማረፍ ምንኛ ጣፋጭ ነው፡፡

ክርስቲያኖች ዘላለማዊ ቤታቸው የሆነውን መንግሥተ ሰማያትን ስለሚያስቡና ወደዚያም ለመግባት ስለሚናፍቁ እጅግ ደስተኞች ናቸው፡፡ ብዙ መኖሪያ ባለበት በአባታችን ቤት ለመሆን (ዮሐንስ 14÷2)፤ ሐዘን፣ ልቅሶ ወይም ሥቃይ በሌለበት ሥፍራ ለመኖር (ራእይ 21÷4)፤ ከወደደን ከእግዚአብሔር አብ ጋር፣ ስለእኛ ከሞተው ከልጁ ከኢየሱስ ጋር እና ወደ መስቀሉ ሥር ካመጣን ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘላለም ለመኖር፤ በምድር ላይ ዙሪያችንን ከሰፈሩት ቅዱሳን መላእክት ጋር (መዝሙር 34÷7) ለዛላለም አብረን ለመሆን እና በጌታ ካንቀላፉ ክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር ለመቀላቀል (1ተሰሎንቄ 4÷13-18)፤ ማለትም እነዚህን ሁሉ በረከቶች በሙላት ለመቀበል ስለሚናፍቁ ክርስቲያኖች ደስተኞች ናቸው፡፡

ክርስቲያኖች ሲሞቱ እጅግ ደስተኞች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሞት ክርስቶስ አማኞችን ወደ ቤቱ፣ ወደ ራሱ

የሚሰበስብበት መንገድ ስለሆነ ነው። ፔይሰን የተባለ ሰው ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ሰዓት ሰማያዊ ከተማ ሙሉ በሙሉ ትታየኛለች። ክብር የተሞላው ብርሃኗ በላዬ ላይ ያንጸባርቃል፤ የነፋስ ሽውታዋም ይታወቀኛል፣ መንፈሷም በልቤ ውስጥ ገብቷል አለ።

# ክርስቶስ ለኀጢአተኞች ያለው ፍቅር

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላዩ ኢየሱስ የጠፋበትን በግ እስከሚያገኘው ድረስ የሚፈልግን መልካም እረኛ አድርጎ ራሱን ገልጿል። ይህ መልካም እረኛ የጠፋበትን በግ ሲያገኝ በደስታ በጫንቃው ላይ በመሸከም ወደ ቤት ይዞት በመመለስ ጓደኞቹን በመጥራት እንዲደሰቱ ያደርጋል፤ የጠፋውን አንድ በጉን አግኝቷልና። አቤት፣ ዛሬም ኢየሱስ በጫንቃው ላይ እንዲሸከምህ ብትፈቅድለት! አንተን ሲያገኝህ በጣም ስለሚደሰት ቅዱሳን መላእክቱን ጠርቶ ከእነርሱ ጋር አብሮ ደስ ይለዋል (ሉቃስ 15÷10)።

ኢየሱስ ለኀጢአተኞች ያለው ፍቅር በምድር በሥጋ በተመላለሰበት ጊዜ ታይቷል። ፍጹም አምላክ የሆነው ኢየሱስ ስለ እኛ ሲል የባሪያን መልክ ይዞ፣ ከድንግል ተወልዶ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም ራሱን ዝቅ አደረገ። ያ ኢየሱስ ዛሬም አለመለወጡን እናስታውስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንት፣ ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው (ዕብራውያን 13÷8)።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ላይ ታሪኳ የተጻፈውን ሴት ተመልከት። ኀጢአተኛ ሆና ወደ ክርስቶስ መጣች። እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ ታርስ፣ በራሷም ጠጉሩን ታብሰውና እግሩን እየሳመች ሽቱ ትቀባው ነበር። ኢየሱስ ኀጢአተኛ ነሽና ከፊቴ ዘወር በይ ብሎ አላባረራትም። ነገር ግን፦ ብዙው ኀጢአቷ ተሰርዮላታል አለ። ይህች ከኀጢአቷ በንስሓ ወደ ኢየሱስ ዘወር ያለች ኀጢአተኛ ሴት በጸጋው በነጻ ምሕረትን አገኘች።

# ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ

ቀረጥ ሰብሳቢና ሰዎችን አስገድዶ በማስከፈል ባለጠጋ የነበረውን ዘኬዎስን ተመልከት። ኢየሱስ ማለት የትኛው እንደሆነ ለማየት ይፈልግ ስለ ነበር፣ ጌታ በሚያልፍበት መንገድ ባለ አንድ የሾላ ዛፍ ላይ ወጣ። ኢየሱስም እዚያ ቦታ ሲደርስ ቀና

ብሎ አየውና፣ ዘኬዎስ ሆይ፤ ፈጥነህ ውረድ። ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል አለው። ዘኬዎስም ከወጣበት ዛፍ ወርዶ በጌታ ፊት በመቆም እንዲህ ሲል ተናገረ፦ ጌታ ሆይ፤ እነሆ ካለኝ ሀብት ሁሉ ግማሹን ለድኾች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ቀምቼ ከሆነ፣ አራት እጥፍ አድርጌ እመልሳለሁ። በዚህ ንግግሩም ዘኬዎስ ልቡ እንደተለወጠና የኀጢአትን ይቅርታ እንዳገኘ መሰከረ (የሉቃስ ወንጌል 19÷1-10)። ኢየሱስ ዛሬም ያው ነው፤ ምሕረትን በመስጠት የሰዎችን ልብ ይለውጣል።

ጌታ ኢየሱስን በሞተበት ቀን የተናገረውን ልብ በል። በመስቀል ላይ በምስማር ከተቸነከረ በኋላ አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ ጸለየ። በዚያን ዕለት ከተከናወኑት አስደናቂ ተአምራቶች መካከል አንዱ፣ በመስቀል ላይ ለመሞት እያጣጣረ የነበረው ወንጀለኛ ጌታን፦ ኢየሱስ ሆይ፤ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ብሎ በመለመኑ ወዲያውኑ ምሕረትን አግኝቶ ለዘላለም ሕይወት መብቃቱ ነው። ለዚህ ልመናው ጌታ ኢየሱስ በፍጥነት የሰጠው መልስ፣ እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ የሚል ነበር። ይህ ወንጀለኛ ሰው በማለዳ በኀጢአቱ ውስጥ እንደተዘፈቀ ነበር፤ ከሰዓት በኋላ በክርስቶስ በማመኑ ዳነ፤ ማታ ደግሞ ከክርስቶስ ጋር በገነት ሆነ። በጥቂት ሰዓት ውስጥ በክርስቶስ ደም ከኀጢአቱ በመንጻት፣ ጸድቆና ተቀድሶ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወረሰ (የሉቃስ ወንጌል 23÷26-43)። ክፉና ወንጀለኛ ለተባሉ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ጸጋው እንዴት የበዛ ነው!

ኢየሱስ በቀራንዮ የተሰቀለበትን ሁኔታ ልብ በል። ለመሆኑ በቀራንዮ ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠውና የሞተው ለማን ነው? ክርስቶስ የሞተው መልካም ነን ለሚሉ ሰዎች ሳይሆን ለደካሞችና ለዒጢአተኞች ሰዎች ነው (ሮሜ 5÷6)። በኢሳያስ 53÷5-6 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ እያንዳንዳችንም በየመንገዳችን ነጐድን፤ እግዚብሔርም፣ የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ጫነው።

ክርስቶስ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ (1ጴጥሮስ 2÷24)። በእነዚያ ሰዓታት በሥጋው የተቀበለው መከራ ከሚታሰበው በላይ ከባድ ሲሆን፤ ከዚያ ሁሉ

በላይ ደግሞ በነፍሱ የከፈለው ዋጋ ወደር የማይገቃለት ነው:: ኀጢአት የሌለበት ክርስቶስ ስለ እኛ ኀጢአት ሆነ (2ቆሮንቶስ 5÷21):: የእኛን ኀጢአት ስለ ተሸከመም በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ሰዓት፣ አምላኬ፤ አምላኬ፤ ለምን ተውኸኝ? (ማቴዎስ 27÷46) እያለ ሲጮኽ አባቱ ፊቱን አዞረበት:: አቤት ይኼ ኢየሱስ ለኀጢአተኞች ያለው ፍቅር እንዴት ልዩ ነው! ይህንን ሁሉ መከራ የተቀበለው ኀጢአተኞችን ለማዳን ሲል ነው::

## ልዩነቱን የፈጠረው ምንድነው?

ከአምስት አመታት በፊት ሁለት ሰዎች በዚህ አገር ይኖሩ ነበር:: ዛሬ ሁለቱም በሕይወት የሉም፤ ሞተዋል:: አንደኛው በመንግሥተ ሰማየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በሲኦል ነው:: በሁለቱም ሰዎች መካከል የነበረው ልዩነት ምንድን ነው? ልዩነቱ የሚከተለው ነው:: አንደኛው ኀጢአተኛነቱ ተነገረው፤ ከኀጢአቱም እንዲያድነው ኢየሱስ ዋጋ እንደ ከፈለለት ተረዳ:: ኢየሱስን እንደግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ በኋላ የቅድስና ሕይወት ኖረ:: ሲሞት ወደ መንግሥተ ሰማያት ገባ::

ሁለተኛው ሰው ወደፊት አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኙ አድርጎ እንደሚቀበል ቢያስብም በወቅቱ ክርስቶስን ወደ ጎን ገፋው:: ጊዜው ሲደርስ ሞተ:: አሁን በሲኦል ሆኖ ታላቁን አዳኙን ክርስቶስን ንቆ በመተው እየተጸጸተና በሀዘን እያለቀሰ ማለቂያ በሌለው ዘላለማዊ ስቃይ ውስጥ ይኖራል:: ጌታን ለመቀበል ገና ጊዜ አለህ የሚለው አባባል ሰይጣን የሚታወቅበት ታላቅ ውሸት ነው::

## ኀጢአት ምንድን ነው?

እስቲ ኀጢአትን ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከእግዚአብሔር ቅድስና አንጻር እንመልከተው:: ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቅድስና ባየ ጊዜ፣ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ፤ - - - ዐይኖቼም ንጉሡን፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔርን አይተዋልና ጠፍቻለሁ፣ ወዮልኝ! አለ (ኢሳይያስ 6÷5):: እግዚአብሔር አፍቃሪ አምላክ ነው፤ ፍቅሩ ግን የቅዱስ አምላክ ፍቅር ነው:: የኀጢአተኞችን በደል ይቅር የሚልበት ብቸኛ መንገድ በክርስቶስ ውስጥ ብቻ እንደሚገኝ ነግሮናል:: ስለዚህም ከክርስቶስ ውጪ በሌላ በማንኛውም መንገድ ኀጢአተኛን ይቅር አይልም::

ኀጢአትን እግዚአብሔር በኀጢአት ላይ ከሚሰጠው ፍርድ አንጻር እስቲ ተመልከተው። እግዚአብሔር ኀጢአትን የቱን ያህል እንደሚጠላና በኀጢአት ላይ ምን ዐይነት ፍርድ እንደሚፈርድ ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን ተመልከት። እግዚአብሔር ኀጢአትን ስለሚጠላ ኀጢአት የሠሩትን መላእክት እንኳ በሙሉ ከመንግሥተ ሰማያት አስወጣቸው። አዳምንና ሔዋንን ከኤደን ገነት አስወጣቸው፤ ነፍስና እስትንፋስ ያለው ፍጥረት በጠቅላላ ከምድረ ገጽ እስከሚጠፉ ድረስ ምድርን በውሃ አጠፋት። በኀጢአት የተበከለችው ይህች ዓለምም አንድ ቀን በእሳት ቀልጣ ትጠፋለች። ለምን? እግዚአብሔር ኀጢአትን ስለሚጠላ ነው።

እስቲ ደግሞ ኀጢአትን ከዘላለማዊ ቅጣት አንጻር ተመልከተው። በማቴዎስ 25 ኢየሱስ ብዙ ሰዎች ወደ ዘላለም ፍርድ ይሄዳሉ በማለት ተናግሯል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልዳኑ ሰዎች በሲኦል ስለሚቀበሉት መከራና በኢየሱስ ያመኑት የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት ስለሚኖራቸው ደስታ በዝርዝር ቀርቦል። መንግሥተ ሰማይም ሆነ ሲኦል ለዘላለም የሚኖርባቸው እውነተኛ ቦታዎች ናቸው።

## የጊዜው ርዝመት ምን ያህል ይሆናል?

የዘላለም ሕይወት ምን ያህል ጊዜ እንደሚረዝም አስበኸ ታውቃለህ? አንድ የታወቁ ጸሐፊ እንደዚህ ብለዋል፦ አንዲት ትንሽ ተባይ ይህንን ዓለም ትንሽ በትንሽ በአፍዋ እየቆነጠረች ሩቅ ወዳለ ኮከብ ይዛ ለመሔድ ተነሣች እንበል። አንድ ጉዞ ለማድረግ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዓመታት ያስፈልጊታል። የማጓጓዝ ሥራዋን አሀዱ ለማለት ተባይዋ ከዛፍ ቅጠል ለመጀመር በማሰቧ፣ ከአንድ ቅጠል ላይ የመጀመሪያውን ጥቂት ሸክም ተሸክማ ፍጻሜ የሌለውን ጉዞውን ጀመረች። ብዙ ሚሊዮን ዓመታት ካለፈ በኋላ ሁለተኛ ዙር ሸክሟን ለመውሰድ ወደ ምድር ተመልሳ መጣች። አንዲቷን ቅጠል በዚህ መልክ አጓጉዛ ከመጨረሷ በፊት እንዴት ያለ ረዥም ጊዜ ይወስድባት ይሆን? ለመሆኑ አንድ ዛፍ በሙሉ በስንት የጉዞ ምልልስ ጊዜ ያልቅ ይሆን? ዱሩንስ ጨርሶ ለማጊጓዣ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል? በዚህ ረዥም ጉዞዋስ መቼ ነው ተባይዋ የመጨረሻውን ብናኝ ከዚህች ዓለም ላይ የምታነሳው? ይህ በሚሆንበት ጊዜ እንኳን ቢሆንም ዘላለም ገና ጅማሬው ይሆናል። የዘላለም ፍርድ ምንድን ነው?

የዘላለም ፍርድ እግዚአብሔር በኀጢአት ላይ ያለውን ጥላቻ የሚገልጥበት መንገድ ነው።

## እነሆ! የእግዚአብሔር በግ

እስቲ ኀጢአትን ክርስቶስ በሞቱ ለኀጢአት ማስተሰሪያ ከከፈለው መስዋዕት አንጻር ተመልከተው። ከክርስቶስ ሞት ውጪ ሌላ ነገር ወይም ከዚያ ያነሰ ነገር ለኀጢአት ማስተሰረያ መስዋዕት ሆኖ ለመቅረብ ቢችል ኖሮ፣ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለሞት አሳልፎ ባልሰጠም ነበር። ኢየሱስ ሦስት ጊዜ፣ አባቴሆይ፤ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፤ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን። (ማቴዎስ 26÷36-44) ብሎ ሲጸልይና በታላቅ ድምፅ አየሩን ሲሰነጥቀው፣ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር እየፈሰሰ አፈሩን ሲያረጥበው የነበረበትን ሁኔታ ልብ በል (ሉቃስ 22÷44)። ኢየሱስ በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታ ሲጮኽ፣ ሥቃዩንም ለመቋቋም እንዲችል በአብ ሲበረታታ፤ እንዴት ዐይነት ከፍተኛ ሥቃይ እንደተቀበለ መረዳት ይቻላል።

ይህ ጽዋ ከኢየሱስ ማለፍ ቢችል፣ ማለትም እኛ ምስኪን የሆንን ኀጢአተኞች ካለ እርሱ ሥቃይ መዳን ብንችል ጩኸቱ መስማቱ አይቀርም። ይሁን እንጂ ይህ የማይቻል ነገር ከመሆኑ የተነሣ ሥቃይ መቀበሉ የማይቀር ነው። እግዚአብሔር በኀጢ አት ላይ ያለውን ጥላቻ የግድ መግለጥ ስለነበረበት አንድያ ልጁ ሥቃይን ይቀበል ዘንድ ኀጢአትን ሥጋው መሸከም ነበረበት። ስለሆነም ኢየሱስ፡- ዎአምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ? (ማርቆስ 15÷34) ብሎ በታላቅ ድምፅ እስኪጮኽ አብ ፊቱን ከወልድ ሰወረ።

ኀጢአትን ከእግዚአብሔር መልካምነትና ላንተ ባለው ፍቅር አንጻር እስቲ ተመልከተው። ጠላትህን ብትመታው ኀጢአት ነው። ወዳጅህን ብትመታው ደግሞ የበለጠ ኀጢአት ይሆንብሃል። ነገር ግን እጅህን አንሥተህ አፍቃሪ አባትህን ብትመታ ከሁሉ የከፋ ኀጢአት ነው። እንደ እግዚአብሔር ጌታ ያለውን መልካሙን አምላክህን ብትቃወመው የቱን ያህል ከሁሉ የላቀ ኀጢአት ትሠራ? ከተወለድክባት ቀን ጀምሮ በአንተ ላይ በፍቅር የተሞላ ርኅራኄውንና ምሕረቱን አላበዛልህምን?

# ኢየሱስ የልብህን በር ያንኳኳል

ኢየሱስ ወደ ውስጥህ ለመግባት፣ ኀጢአትህን ለማስወገድ፣ በመንፈሱ አማካኝነት በውስጥህ ለመኖር፣ ቅዱስ ሊያደርግህ ስለፈለገ የልብህን በር አንኳኩቷል። ሌሎች ክርስቲያኖች ስለ አንተ በሚጸልዩት ጸሎት ልብህን አንኳኩቷል። በአስተማሪዎችህ ምክርና ትምህርት የልብህን በር አንኳኩቷል። ቅን በነበርክበት በዚያች ሰዓት የልብህን በር አንኳኩታል፤ ወንጌልን በመስበክ ደጋግሞ በርህን አንኳኩቷል ጓደኞችህ ኢየሱስን አምነው ሲለወጡ አንኳኩቷል። በበሽታ ውስጥ ሆነህ አንኳኩቷል። እንደነዚህ ዓይነት የመዳን አጋጣሚዎችን በሰጠህ አምላክ ላይ የሰራኸው ኀጢአት እንዴት ብዙ ነው!

ኀጢአትህን በተለይ ክርስቶስን ላለመቀበል ካነሣኸው ተቃውሞ አንጻር እስቲ ተመልከተው። ከኀጢአቶች ሁሉ የላቀው ማለትም ለእርግማን የሚዳርገው ኀጢአት ክርስቶስን አምኖ አለመከተል ነው። አንተን ፈልጐ በማግኘት እንዲያድንህ እግዚአብሔር ልጁን ልኳል (ሉቃስ 19÷10)። ክርስቶስ ለኀጢአተኞች ሲል በመሞቱ እግዚአብሔር በመርካቱ፣ ስለ ክርስቶስ ሲልም ኀጢአተኞችን ይቅር በማለቱ እጅግ ደስ ይለኛል። ሆኖም እስከዚህች ደቂቃ ድረስ ልጁን ክርስቶስን በማመን የግል አዳኝህ አድርገህ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆንክም። አቤት! ይህ ክርስቶስን ያለመቀበልህ አንተ አዳኜ እንድትሆን አልፈልግም ማለትህ እንደሆነ ቢገባህ እንዴት ጥሩ ነበር (ዕብራውያን 10÷26-31)።

በአንድ ምሽት ሦስት ጊዜ በመደጋገም ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም በማለት ተናግሮታል (ዮሐንስ 3÷1-2)። አንባቢዬ ሆይ! ዳግመኛ ተወልደሃልን? አዲስ ልደት የሚባለውንና የሕይወት ለውጥ የሚያመጣውን ልምምድ ቀምሰኸዋልን? ክርስቶስን አምኖ ለመከተል የውሳኔ ዕርምጃ ስትወስድ ዳግመኛ ትወለዳለህ፣ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው (ዮሐንስ 1÷12)።

# የጠፋች ነፍስ

መጽሐፍ ቅዱስ፣ የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና ደግሞም ኀጢአት የምትሠራ ነፍስ ትሞታለች ይላል። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ሞት በኀጢአት ምክንያት በጠፋው ኀጢአተኛ ላይ እግዚአብሔር የሚያመጣውን ሥቃይ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።

ጌታ ኢየሱስን አምኖ የግል አዳኙ አድርጎ ያልተቀበለ ኀጢአተኛ በሙሉ አሁን በአካለ ሥጋ ቢኖርም እንኳን አሁኑኑ ተፈርዶበታል (ዮሐንስ 3÷18)። ኢየሱስ ክርስቶስን አምነህ አልተቀበልክ እንደሆነ ነፍስ በመግደል ወንጀል ሞት ተፈርዶበት በእስር ቤት ውስጥ የሞት ፍርዱን የሚቀበልበትን ሰዓት በመጠ ባበቅ ላይ እንዳለ ወንጀለኛ ነህ። የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነው ሞት ድንገት ሊወስድህ በማንኛውም ሰዓት ይመጣል።

የእግዚአብሔር ቁጣ በላይህ ላይ ነው (ዮሐንስ 3÷36)። እግዚብሔር በየዕለቱ በክፉ ሰው ሥራ ላይ የቁጣ ክንዱን ይሰነዝራል።

የዲያብሎስ ልጅ እንዲሁም ተገዥ ባሪያው ነህ። ዲያብሎስ ደግሞ የእግዚአብሔርና የሰው ልጅ ትልቁ ጠላት ነው። ነፍስህንና ሥጋህን ለማጥፋት በየቀኑ ይተጋል። ጌታህ ስለሆነም በየዕለቱ የምታከናውነው እርሱ እንድትሠራ የሚፈልገውን ነው። እርሱም አሉ ከሚባሉ ጌቶች ሁሉ እጅግ ጨካኝ ጌታ ነው።

አንድ ቀን መሞትህ አይቀርም፤ አሟሟትህ ደግሞ ድንገተኛና በቅርቡ የሚሆን ነው። ስትሞት ምን ይሆናል? በሞተው ኀጢአተኛ አልጋ ዙርያ ጋኔኖች ይቆማሉ። ሰውየው እንደሞተ ወድያውኑ ነፍሱን ተሸክመው ወደ ገሃነም ወደ ጥልቁ ይወስዱታል።

የእግዚአብሔርን የመለከት ድምፅ የምትሰማበት ቀን ይመጣል፤ ያን ጊዜ ከመቃብርህ ትወጣለህ። ክርስቶስን ሳታምን ሞተህ ከሆነ የተረገመችው ነፍስህ ወደ ተረገመው ሥጋህ ትገባና በጌታ የፍርድ ወንበር ፊት ትቆማለህ።

የእግዚአብሔር መጽሐፍ ይከፈታል። በተሰበሰበው የሰው ዘርና መላእክት ፊት እያንዳንዷ የተናገርካት ክፉ ቃልና እያንዳንዱ የሰራኸው ክፉ ሥራ በአለም ሕዝብ ፊት ይነበባል። ከዚያም የኢየሱስ ድምጽ፣ አንተ የተረገምህ፤ ለዲያቢሎስና

ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይተህ ሂድ፤ ሲል ትሰማዋለህ (ማቴዎስ 25÷41)።

# ይህ ለዘላለም ይሆናል

እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ ... ይሄዳሉ (ማቴዎስ 25÷46)። አዎን፣ እግዚአብሔርን ከሚፈሩ አባትህና እናትህ፣ ከምትወዳቸው ሰዎች፣ ከቤትህ፣ ከእረፍት ስፍራህ፣ ከስብሰባዎችህ ተለይተህ ወደ ዘላለም ፍርድ ትሄዳለህ።

ከፍተኛ ስቃይ በምትቀበልበት ቦታ ስለምታገኛቸውና ስለሚበሉህ ትሎች እስቲ ጥቂት እናስብ። ከትሎቹ አንዱ በሲኦል ሆነህ ልታረካው የማትችለው ክፉ ምኞቶችህ ናቸው።

ሌላው ትል ትዝታህ ነው። ለእግዚአብሔር መንግሥት ቅርብ የነበርክባቸውን ጊዜያት ያስታውስሃል። አሁን ግን ለዘላለም ጠፍተሃል።

ቀጣዩ ትል በስቃይ ቦታህ ከአንተ ጋር የምታገኛቸው አስጨናቂ የሆኑ ክፉና አስፈሪ ፍጥረታት ናቸው። በዚህ ስፍራ ወደ ኀጢአት የመራሃቸውን ሰዎች ስለምታገኛቸው፤ ለለዘላለም ሲረግሙህ፣ ሲቆጡህ፣ የስድብ መአት ሲያወርዱብህ ይኖራሉ።

ይህም ለዘላለም ይሆናል። ይሄ የመርገም መርዝ፣ የመርገም ቃጠሎ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «የሥቃያቸውም ጢስ ከዘላለም እስከ ዘላለም ወደ ላይ ይወጣል» ይላል (ራእይ 14÷11)። ከሚሊዮን ዓመታት በኋላ ነጻነትን የማግኘት ተስፋ ቢኖርም እንኳ፣ በሲኦል ግን ፈጽሞ አይኖርም። በሲኦል ውስጥ ምንም ተስፋ የለም። አቤት የዘላለም ሕይወት! ዘላለም ሕይወት! ማለቂያ በሌለው ሕይወት በሲኦል ለዘላለም መኖርን አስበኸው ታውቃለህ?

# ከዚያስ በኋላ ምን?

አንድ ቀን በዩንቨርሲቲ ውስጥ አንድ ወጣት ለፕሮፌሰሩ ስለወደፊት ሕይወቱ ያለውን እቅድ ይነግራቸው ነበር። የሕግ ምሑር ለመሆን እንደሚፈልግም ገለጻላቸው። ፕሮፌሰሩም ከዚያስ በኋላ ምን ታስባለህ? ሲሉ ጠየቁት ፕሮፌሰሩም። እርሱም ከዚህ በኋላ ለዶክትሬቴ አጠናለሁ ሲል መለሰላቸው። እርሳቸውም ከዚያስ በኋላ? ሲሉ በድጋሚ ጠየቁት። እርሱም ከዚያ በኋላ በጣም አስቸጋሪ የሚባሉ ክሶችን ተከታትየ ውሳኔ እንዲያገኙ በማድረግ ዝነኛ እሆናለሁ አለ። እርሳቸውም እንደገና ከዚያስ

በኋላ ምን ትሆናለህ? አሉት፡፡ እርሱም ከዚያ በኋላ ከፍ ያለ ማዕረግ ወዳለው ሌላ ቢሮ እሾምና ባለጠጋ እሆናለሁ አለ፡፡ እንደገናም ፕሮፌሰሩ፣ ከዚያስ በኋላ? ሲሉ ጠየቁት፡፡ እርሱም፣ ከዚያ በኋላ ባለጠጋና የተከበረ ሰው በመሆን እኖራለሁ አለ፡፡ እንደገናም፣ ከዚያስ በኋላ? አሉት፡፡ እርሱም፣ ከዚያ በኋላ . . . ከዚያ በኋላ . . . ከዚያ በኋላ እሞታለሁ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ፕሮፌሰሩ ድምጻቸውን ከፍ አደርጉና ጮክ ብለው ጠየቁ፣ ከዚያስ በኋላ ምን? አለ፡፡ አሁን ወጣቱ ምንም መልስ አልሰጠም ነገር ግን አንገቱን አቀርቅሮ ትቷቸው ሄደ፡፡ ከዚያ ብዙም ሳይቆይ ራሱን ለክርስቶስ በመስጠት የተቀደሰና ትርጉም ያለው ሕይወት መኖር ጀመረ፡፡

## በክርስቶስ የተገኙ 14 በረከቶች

ክርስቶን የግል አዳኝ አድርገህ በምትቀበልበት ጊዜ የምታገኛቸውን በረከቶች እንድታውቅ እፈልጋለሁ፡፡ ከዓመታት በኋላ የምታገኘውን ሳይሆን፤ ነገር ግን ኢየሱስ የግል አዳኝህ እንደሆነ በምታምንበት ቅጽበት ከመብረቅ ብልጭታ ባላነሰ ፍጥነት ውስጥ ወዲያውኑ የምታገኛቸውን በረከቶች እነግርሃለሁ፡፡ እነዚህ በረከቶች የሚሰጡህ ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታደርገውን ጉዞ እንድትጀምርና እንድትፈጽም ይረዱህ ዘንድ ነው፡፡

1. ለሠራኸው ኀጢአት ሁሉ ሙሉና ነጻ የሆነ ምሕረት ትቀበላለህ፡፡ የኀጢአት ይቅርታ የሚገኘው በኢየሱስ በኩል መሆኑ እንደ ተሰበከላችሁ ዕወቁ፤ በእርሱ የሚያምን ሁሉ በሙሴ ሕግ በኩል ማግኘት ያልተቻለውን ጽድቅ ያገኛል (ሐዋርያት ሥራ 13÷38-39) በእርሱ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ ጥቂቶች ሳይሆን የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቃሉ፡፡ ይህም ማለት በነጻ ምሕረትን ተቀብለዋል ማለት ነው፡፡
2. ኀጢአትህ ከአንተ ተወግዷል፡፡ እግዚአብሔር ኀጢአትህን ዳግመኛ በማያይበት ሁኔታ ወደ ኋላው ጥሎታል ማለት ነው (ኢሳያስ 38÷17)፡፡ እንደገናም ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ መተላለፍችንን በዚያው መጠን ከእኛ አስወገደ ይላል (መዝሙር 103÷12)፡፡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያለው ርቀት ምንያህል ነው? ከዚህም በላይ፣ኀጢአታቸውንና ዐመጻቸውን፣ ከእንግዲህ አላስብም ይላል (ዕብራውያን 10÷17)፡፡

3. በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝተሃል፡፡ ቁጣው ከአንተ ተመልሶ በሚወደው ልጁ በኩል ተቀባይነት አግኝተሃል (ኤፌ 1÷4-8)፡፡

4. የአንተ ኀጢአት በሙሉ በክርስቶስ ላይ ሲደረግ፣ የእርሱ በጎ ሥራ ሁሉ ለአንተ ስለተሰጠ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድትሆን ተደርገሃል (2ቆሮ 5÷21)፡፡

5. የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል፤ እግዚአብሔር አባትህ ነው፡፡ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው (ዮሐ 1÷12)፡፡

# የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ተጠራን

6. እግዚብሔር ይወድሃል፤ አንተን በመምራት፣ በመጠበቅ እና የሚያስፈልግህን ሁሉ በመስጠት ደስ ይለዋል፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ጸልዮልሃል፣ አንተ እንደ ላክኸኝና እኔን በወደድኸኝ መጠን እነርሱንም እንደ ወደድሃቸው ዓለም ያውቅ ዘንድ (ዮሐ 17÷23)፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር ምንኛ ታላቅ ነው (1ዮሐ 3÷1)፡፡

7. በውስጥህ እንዲኖርና የቅድስና ሕይወት ለመኖር እንዲያስችልህ መንፈስ ቅዱስን ትቀበላለህ፡፡ አቤቱ አንተ ደካማ አማኝ ብትሆንም እንኳ እግዚብሔር በአንተ ውስጥ ይኖራል፡፡ የእግዚብሔር ቤት መቅደስ እንደሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? (1ቆሮ 3÷16)፡፡

8. አዲስ ልብ ይሰጥሃል፤ አዲስ ፍጥረትም ትሆናለህ፡፡ አዲስ ልብ እሰጣችኋለሁ፤ አዲስ መንፈስም በውስጣችሁ አሳድራለሁ (ሕዝቅኤል 36÷26)፡፡ ፈቃዱን እንድታውቅ፣ ፈቃዱን እንድትወድና ፍቃዱን እንድታደርገው ብቃትን ይሰጥሃል፡፡

9. ለሠራኸው ኀጢአት ሁሉ ንስሓን የመግባትንና ስለኀጢአትህ በእውነት የመፀፀት ችሎታን ታገኛለህ፡፡ እርሱም ለእስራኤል ንሰሓንና የኀጢአትን ስርየት ይሰጥ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ራስና አዳኝ አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው (የሐዋርያት ሥራ 5÷31)፡፡

10. ክርስቶን ለመውደድ ኀይል ታገኛለህ፡፡ እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛም እንወደዋለን (1ዮሐንስ 4÷19)፡፡ ፍቅር

ፍቅርን ይወልዳል:: እርሱ ለአንተ ያለውን ፍቅር አብዝተህ በተመለከትህ ቁጥር እርሱን የበለጠ ትወደዋለህ::

11. በኢየሱስ ስም የመጸለይ ኀይል ታገኛለህ:: የክርስቶስ መልካም ባህርያትና ሥራዎች በአንተ ስላሉ፣ በስሙ ወደ አብ መቅረብና ቃል ኪዳኖቹ በሕይወትህ እውን እንደሆኑ መጠየቅ ትችላለህ::

# የማይመረመረው የክርስቶስ ባለጠግነት

12. መልካም ሥራ ለመሥራትና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚያስችል ኀይል ታገኛለህ:: እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት በመጀመሪያ መሥራት ያለብህ ሥራ ክርስቶስን የግል አዳኝህ አድርገህ መቀበል ነው:: ከዚያ በኋላ የምትሠራው ሥራና የምትሰጠው አገልግሎት ሁሉ የተሟላና እርሱን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል::

13. እጅግ ውድ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች ሁሉ የአንተ ይሆናሉ:: ከእግዚብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣ አዎን የሚሆኑት በእርሱ ነውና፤ እኛም በእርሱ አማካይነት ለእግዚአብሔር ክብር፣ አሜን የምንለው በዚህ ምክንያት ነው (1ቆሮንቶስ 1÷20):: በነዚህ የተስፋ ቃሎች ውስጥ ያለው በረከት እንዴት እስደናቂ ነው!

14. የዘላለም ሕይወትን ታገኛለህ:: ኢየሱስ የሚከተሉትን ቃላት ተናግሯል፣ እውነት እላችኋለሁ፤ (በእኔ) የሚያምን ሁሉ የዛላለም ሕይወት አለው (ዮሐንስ 6÷47):: መንግስተ ሰማያት መኖሪያህ ይሆናል፤ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው ሄጄም ስፍራ ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ (ዮሐንስ 14÷2-3)::

ክርስቶስን የግል አዳኝህ አድርገህ በምትቀበልበት ጊዜ ወዲያውኑ እነዚህን በረከቶች በሙሉ ታገኛለህ:: ጳውሎስ ስለማይመረመረው የክርስቶስ ባለጠግነት የተናገረው ይህ ነው (ሮሜ 11÷33):: በጊዜው ፈንድቶ በሚፈካው እምቡጥ የጽጌረዳ አበባ ውስጥ በጣም አስደናቂ የሆነ ውበት፣ ቀለምና መዓዛ ተሸሽጎ ይገኛል:: በክርስቶስ ውስጥ ያሉት ሀብቶች እንዴት የማይመረመሩ ናቸው!

ጌታ፣ ምንም ነገር ቢኖረን ያለ አንተ ድሆች ነን፤
በአንተ ባለጠጎች ነንና፣ ያሰኘህን ከእኛ ውሰድ።

# ድነት ለሁሉም ሰው በነጻ የተሰጠ ነው

የኖኅ መርከብ ተሠርታ ባለቀችበት ጊዜ ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ ለመዳን ወደ መርከቡ መግባት፣ አለበለዚያ ወደ መርከቡ ባለመግባት በጥፋት ውሃ መጥፋት ነበረባቸው። ነገሩ የአንድ እርምጃ ጉዳይ ነው፤ ስለዚህ ለመዳን እርምጃ መውሰድ ነበረበት (ዘፍጥረት 7-9)።

የሞት መልአክ የግብፃውያንን በኩር ለማጥፋት በግብፅ ምድር ላይ ሁሉ በወጣ ጊዜ፣ በየበሩ ጉበንና መቃን ላይ ያለውን ደም ሲያይ፣ ያንን ደጃፍ እያለፈ ይሄድ ነበር (ዘፀአት 12÷21-23)፤ እኛም እንዲሁ ከመጥፋት እናመልጥ ዘንድ በልባችን ላይ እንደዚሁ የክርስቶስ ደም መረጨት አለበት (ዕብ 10÷22)።

የሚቃጠል መሥዋዕት ኀጢአትን ለማስተሰረይ እንደሚቀርብ ሁሉ (ዘሌዋውያን 6÷8-13)፤ እኛም በቅንነትና በእውነተኛነት ኀጢአቶቻችንን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ፣ በኢየሱስ ላይ መተው ይጠበቅብናል (1ዮሐንስ 1÷8-10)፤ ይህ ካልሆነ መዳን አንችልም።

ኢየሱስ ለኀጢአት ማስተሰረያ የሞተውን ሞት አምነህ የኀጢአት ስርየትን መቀበል የምትችለው እንዴት ነው? ታማኝ በሆኑት የተሰፋ ቃሎቹ ላይ በመደገፍ በእምነት በመቀበል ነው። በዚህች ጊዜ እንኳን ኢየሱስ ለኀጢአቶችህ በሙሉ ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ሞቱን አቅርቦልሃል።

ምሕረትን መቀበል ማለት በቀላሉ ለእርሱ ኀጢአትን በሙሉ መናዘዝ ማለት ነው፤ ከዚያም ጌታ ኢየሱስ፣ ኀጢአቴን ለማስተሰረይ ሞትህን ስጦታ አድርገህ አቅርበህልኛል። አሁን በዚህ ጊዜ ስጦታህን እቀበላለሁ፤ ሞትህን ለኀጢአቴ ማስተሰረያ፤ አንተንም የግል አዳኜ አድርጌ እቀበላለሁ ብለህ መጸለይ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ ድኻ የሆነ ደካማ ሰው ከባድ ሸክም ተሸክሞ በመንገድ ላይ ይሄድ ነበር። በመጓዝ ላይ ሳለ አንድ ብርቱ ሰው ወደ እርሱ ቀረብ ብሎ፣ የተሸከምከው ሸክም ለአንተ በጣም ከባድ ነው፤ ለእኔ ስጠኝና እሸከምልሃለሁ፣ ከእርሱም አሳርፍሃለሁ አለው። በዚያን ጊዜ ያ ደካማ ድኻ ሰው ሸክሙን

ለብርቱው ሰው አስረከበው። እንደዚሁም እኔ የኀጢአቴን ከባድ ሸክም ተሸክሜ ሳለ ኢየሱስ መጣና፣ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉትዋ አለኝ (1ጴጥሮስ 5÷7)። እኔም የኀጢአቴን ሸክም ሁሉ ለእርሱ ሰጠሁት፤ እርሱም ከእኔ ወሰደው።

ቀና በሆነ እምነት እርሱን ብትፈልገው ብዙም ሳትቆይ በደስታ ነፍሴ የወደደችውን አገኘሁት ትላለህ (ማሕልየ መሓልይ 3÷4)። 2ቆሮንቶስ 5÷20-21 እንደዚህ ይላል፣ ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴዎች ነን፤ እግዚብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው። ኢየሱስ ስለ እኛ ኀጢአት ተደረገ፤ እኛ በእርሱ የእግዚአብሔር ጽድቅ ሆንን፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንድንታረቅ ይለምነናል፤ ኢየሱስ ስለ እኛ ይጸልያል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ስጦታ በእምነት እንድንቀበል የሚያበረታታ እንዴት ያለ የተስፋ ቃል ነው።

# መሰረተ ቢስ ፍርሀቶች

ኀጢአቴ ይቅር ሊባል የማይችል እጅግ ታላቅ ነው ብለህ በማሰብ ትፈተን ይሆናል። ነገር ግን የክርስቶስን መከራ አስብና እግዚአብሔር፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል (1ዮሐንስ 1÷7) ያለውን ቃል አምነህ ተቀበል።

በ1ቆሮንቶስ 6÷9-10 ላይ የተጻፈውንና የሚከተለውን ቃል ልብ በል፤ ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፣ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን፣ ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱምዋ። እንዴት የሚያስፈራ ዝርዝር ነው!!

ማንበብህን አታቁም የሚከተለውን አስተውል፤ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል (1ቆሮንቶስ 6÷11)። እነዚህን ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስታነብ ጊዜ የራስህንም ሆነ በሕይወት

ያለን የሌላ ሰው መዳን በፍጹም አትጠራጠር:: ስለማንነትህ ማሰብ ትተህ ኢየሱስ እንዴት ያለ ድንቅ አዳኝ እንደሆነ አስተውል::

# የእምነት ውሳኔ የሚደረግበት ወቅት

በቅርብ ጊዜ ከአንድ ወጣት ጋር በመንገድ እሄድ ነበር:: በክርስቶስ አምኖ በምን ሁኔታ ክርስቲያን ለመሆን እንደቻለ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት:: እንዲህ አለኝ፣ የአክስቴ ልጅ ደብዳቤ ጽፋ ቤቷን እንዳይላት ስለጠየቀችኝ ልጎበኛት ሄድኩ:: የአክስቴ ልጅ ስለ ነፍሴ ጉዳይ በቀጥታ አላነሳችብኝም፤ ነገር ግን አንዲት ሌላ ወጣት ሴት ክርስቶስን በማመን ክርስቲያን የሆነችበትን ሁኔታ እንዲህ ስትል ተረከችልኝ፤ ይህች ወጣት ለመዳንና የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን እጅግ በጣም ትፈልግ ነበር፤ ነገር ግን በራሷ ሥራና ጥረት ራሷን ልታድን እንደማትችል ገብቷት ነበር::

ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ስለመተላለፍዋ እንደቆሰለ እና ስለ በደልዋ እንደ ደቀቀ፣ እንደዚሁም በመስቀል ኀጢአቷን በገዛ ሥጋው ላይ እንደተሸከመ አስተዋለች:: ኢየሱስ ኀጢአቷን ሁሉ እንዲቀበለው ከፈቀደችለት ለኀጢአቷ የሚገባትን ቅጣት መቀበል እንደሌለባት አስተዋለች፤ ኢየሱስ ሥራውን ፈጽሞታልና!

ጌታ ኢየሱስ ሆይ አመሰግንሃለሁ:: ሞትህ ለኀጢአቴ ማስተሰረያ መሆኑን ተረድቼ ተቀብዬዋለሁ፤ አንተንም የግል አዳኜ አድርጌ ተቀብዬሃለሁ ብላ መፀለይ ብቻ እንዳለባት አወቀች:: ምሕረትን ለማግኘት በክርስቶስና በሞቱ ላይ አረፈች:: በዚህን ጊዜ በኢየሱስ የነበራትን ደስታ ብታየው ኖሮ እንዴት ጥሩ መሰለህ:: ቆይታም እንዲህ አለችኝ፤ ስማ ቶማስ አሁን ኀጢአትህ ሁሉ ይቅር እንደተባለ ለማወቅ አትሻም? እኔም ለመዳን ጽኑ ፍላጎት ነበረኝና ሁለታችሁም በጉልበታችን ተንበርክከን እርሷ መጸለይ ጀመረች:: ወዲያው በክርስቶስ ላይ እንዳረፍኩ አመንኩኝ፤ ከተንበረከኩበትም ተነስቼ በጩኸት አምናለሁ! አምናለሁ! ለማለት ውስጤ ተገፋፋ:: ነገር ግን ሰይጣን፣ ሞኝ አትሁን የተሳሳተ ሐሳብ ነው፤ ተራ ስሜት ነው የሚያልፍ ደስታ ነው? ብሎ ጆሮዬ ላይ ያንሾካሾከ መሰለኝ::

ከዚያም የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጤ እንደገና መስራት ጀመረ፤ ክርስቶስም ኀጢአቴን ለመውሰድ እና እኔን ለማዳን ፈቃደኛ እንደሆነ አሳየኝ:: ከተንበረከክሁበት ተስፈንጥሬ

በመነሣት አምናለሁ! አምናለሁ! ብዬ በደስታ ተናገርኩ። የአክስቴም ልጅ ተነስታ አብራኝ በጌታ መደሰት ጀመረች።

የጠላትን ዘዴና እኔን እንዴት አድርጎ ሊያታልለኝ እንደሚሞክር ትነግረኝ ጀመረች፤ ቶማስ አለችኝ፤ ነገ ጠዋት ጠላት ይሄ ሁሉ ያልተጨበጠንና ተራ ሐሳብን ማመን እንደሆነ ይነግርሃል። ከሰይጣን ጋር ስትዋጋ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃልን የመሠለ የጦር መሣሪያ የለህም። ስለዚህም እንደዚህ ብለህ ንገረው ክርስቶስ እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአቶችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ (1ጴጥሮስ 2÷24)፤ ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም (ዮሐንስ 6÷37)። ዛሬ በክርስቶስ ላይ እንደተደገፍክና ወደፊትም በክርስቶ ላይ እንደምትደገፍ ንገረው።

ሰይጣን ክፉ ሐሳቦችን ወደ አእምሮዬ በማምጣት እንደ ቀድሞው መጥፎ ሰው እንደምሆንና ወደፊትም እንደምወድቅ እንደሚነግረኝ አስጠነቀቀችኝ። ይህ ሲሆን ለሰይጣን በራሴ መቆም እንደማልችል እርግጥ እንደሆነና ነገር ግን አዳኜ ኢየሱስ ከመውደቅ ሊጠብቀኝ ቃል እንደገባልኝ (ይሁዳ 24) እና ስሙንም ኢየሱስ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና (ማቴዎስ 1÷21) ተብሎ እንደጻፈ እንድነግረው መከረችኝ።

በኋላም ለወንድሜ ስለ ኢየሱስ የተማርኩትን ነግሬው ከዚያም እርሱ ብዙ ሳይቆይ ተለወጠ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንዳችን ለሌላችን ታላቅ መጽናኛ ሆነናል። አሁን በሕይወት የሌላቸው ታናሽ እህቴም እንደዚሁ ወዲያውኑ በዚያ ጊዜ ክርስቶስን በማመን ክርስቲያን ሆነች።

ውድ አንባቢዬ! ክርስቶስ ለኀጢአተኞች በመስቀል ላይ በከፈለው ዋጋ እግዚአብሔር በመርካቱ ስለ ክርስቶስ ሲል በዚህች ደቂቃ ኀጢአትህን ይቅር ሊል ፈቃደኛ መሆኑን ተረዳህን? ክርስቶስን ለመቀበል ፈቃደኛ ከመሆን ውጪ ለኀጢአትህ ማስተሰረያ እንዲሆን ልታቀርበው የምትችለው ምንም ዓይነት መስዋዕት የለህም። ክርስቶስ አሁን በአጠገብህ ሆኖ ኀጢአትህን ሊወስድና ሊሸከምልህ እየለመነህ ነው።

የሚለምንህን አድርግ እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔኑ፤ እኔም እረፍት እሰጣችኋለሁ (ማቴዎስ 11÷28)። አሁን ወደ እርሱ ና።

# መጽሐፍ ቅዱስ

ይህ መጽሐፍ የያዘው የእግዚአብሔርን ሐሳብ፣ የሰውን ማንነት፣ የድነትን መንገድ፣ በኀጢአተኞች ላይ የሚመጣውን የዘላለም ፍርድ እና የአማኞችን ደስታ ነው።

አስተምህሮዎቹ የተቀደሱ ናቸው፣ ሕግጋቱ መፈጸም የሚገባቸው በውስጡ የሰፈሩት ታሪኮቹ እውነተኛ እና ወሳኔዎቹ የማይለወጡ ናቸው። ጥበበኛ ለመሆን አንብበው፣ ደህንነትን ለማግኘት እመነው፣ ቅዱስ ለመሆን ደግሞ ታዘዘው።

የሚመራህን ብርሃን፣ የሚያሳድግህን ምግብ እና የሚያበረታታህን መጽናኛ ይዟል። መጽሐፍ ቅዱስ የተጓዥ ካርታ፣ የመንገደኛ በትር፣ የአውሮፕላን አብራሪ ኮምፓስ፣ የወታደር ሰይፍ እና የክርስቲያን መመሪያ ነው።

# በኢየሱስ በማመን የሚገኝ ቅድስና

መቀደስ እውን የሚሆነው በአማኙ ልብ ውስጥ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ይህንን የሚያደርገው እንዴት ነው? የአማኙን ዐይን ሕያው አፍቃሪ ወደ ሆነው ወደ አዳኙ በመመለስ ነው። በሮሜ መጽሐፍ ላይ ጳውሎስ፣ ለዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል? በማለት ይጠይቃል። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶ በኩል ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን የሚል መልስ ይሰጣል (ሮሜ 7÷24-25)።

ክርስቲያን በመሆን እንዴት እንደተለወጥህ ታስታውሳለህ? የሕይወትህ ለውጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነበር፤ ኢየሱስ ለኀጢአተኞች በመስቀል ላይ ወደ ሞተው ሞት ዐይኖችህን ዘወር አደረገና አንተን ለማዳን ክርስቶስ የቱን ያህል ፈቃደኛ እንደሆነ አሳየህ። በዳንክበትም ደቂቃ ስለ ክርስቶስ ማሰብ ጀመርክ።

የእግዚአብሔር መንፈስ ሲቀድሰን ዐይኖቻችንን ወደ ክርስቶስ ያዞራል። ጳውሎስ ምን ያድነኛል? ብሎ አልጠየቀም። ሊያድነን የሚችል ምንም ነገር የለም፤ ነገር ግን ሕያው፣ አፍቃሪ የሆነ ሊያድነን የሚችል ማን ተብሎ የተጠየቀለት አንድ አለ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን።

በ1ቆሮንቶስ 1÷30 ላይ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱም ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል። የሚል ተመሳሳይ ሐሳብ ተጽፎልናል። እኛ በክርስቶስ ነን፣ ክርስቶስም በእኛ ውስጥ ነው። የራሳችን ጥበብ የለንም፣ ክርስቶስ ግን ጥበባችን ነው። ጽድቅ የለንም፣ ነገር ግን የክርስቶስ ጽድቅ ልክ እንደ ጸሐይ ብርሃን በነጻ ተሰጥቶናል። በራሳችን የቅድስና ምንጭ የለንም፣ ነገር ግን ክርስቶስ ቅድስናችንና ቤዛችን ነው።

ኢየሱስን ለመቀበል በቻልክባት ቅጽበት ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነሃል። ኢየሱስ ሞተ፣ አንተም በእርሱ ውስጥ ሞትክ። ክርስቶስ ሕያው ሆኖ ይኖራል፣ አንተም በእርሱ ውስጥ ሕያው ነህ። ለኀጢአት እንደሞትክና ከክርስቶስ ጋር እንደተነሳህ ራስህን ቁጠር (ሮሜ 6÷1-11)። ክርስቶስን ልበሰው። በአንተ ውስጥ ይኖር ዘንድ ፍቀድለት። ከእርሱ ጋር ኅብረት አድርግ፤ አነጋግረው፤ ድምፁን ስማ። ውደደው። በእርሱኑር፤ በዚህን ጊዜ ኀጢአት ከአንተ ላይ ተቆርጦ ይወድቃል። ክርስቶስን በውስጧ የያዘች ነፍስ ከኀጢአት ባርነት ተላቅቃለች፤ ነጻ ናት።

# ኢየሱስ እውነተኛው የወይን ግንድ

ክርስቶስ እውነተኛ የወይን ተክል ሲሆን፣ አንተ ደግሞ ቅርንጫፍ ነህ (ዮሐንስ 15)። ለቅርንጫፉ ሕይወትና ጥንካሬ መስጠት የወይን ተክሉን ያስደስተዋል። ቅርንጫፍ ከፍተኛ ጥረትና ትግል በማድረግ በራሱ አድጎ ፍሬ አያፈራም። በወይን ተክሉ ላይ ብቻ ተጣብቆ በመኖር የሚያስፈልገውን ምግብና ጥንካሬ ከሥሩ ይወስዳል። ስለሆነም ኢየሱስ ለእኛ ለቅርንጫፎቹ በየደቂቃው ጸጋንና ኃይልን በመስጠቱ ደስ ይሰኛል።

የመንፈሱን መላት እንድናገቃ ለእያንዳንዳችን ዋጋ የከፈለልን ኢየሱስ በዚህ አለ። በየጊዜው ደጋግሞ እኛን በመንፈሱ መሙላት ያስደስተዋል። በመንፈስ ተሞሉ (ኤፌሶን 5÷18) ብሎ የሚያዝዘንም አሁን ሊሞላን ስለፈለገ ነው። ስሜት ቢኖረንም ባይኖረንም እንደሚሞላን ማመን የለብንምን? በዚህ መልኩ የእምነት እርምጃ ብንወስድ እግዚአብሔር አሁን ከምንለማመደው የላቀ አዲስ ነገርን በሕይወታችን ለማድረግ ረዥም ጊዜ አይወስድበትም።

የተሰጠንን ይህንን መብት እንዴት መጠቀም እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል። የተሰጠንን ጸጋ ካልተጠቀምንበት በስተቀር

ቀን በቀን፣ ሰዓት በሰዓት በክርስቶስ ላይ በመደገፍ ልንኖር አንችልም፡፡ ወንጌል በታማኝነት የሚሰበክበት ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ይኖርብናል፡፡ በዚያም ቦታ በሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎቶች መሳተፍና በሚሠራውም ሥራ መተባበር ይጠበቅብናል፡፡ ምንጊዜም ቢሆን እድሉ ባጋጠመን ቁጥር የጌታን እራት መውሰድ ይገባናል፡፡ ፈተና ወደሚያመጡብን ቦታዎች መሮጥ ይብቃን፤ ክፉ ጠባይ ካላቸው እና ባህሪያቸው ከሚጎዳን ሰዎች ጋር ወዳጅነት አንመስርት፡፡

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱሳችንን በጸሎት ማንበብ ይኖርብናል፡፡ ጂዮርጅ ምዩለር የተባለ የእግዚአብሔር ሰው ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ አጋጣሚውን በመጠቀም መጽሐፍ ቅዱስን ከጸሎት ጋር የማንበብን አስፈላጊነት በአድማጮቹ ልብ ውስጥ ለማኖር ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ በእርግጥ ያለ እግዚአብሔር ቃል በጸጋ ማደግ አንችልም፡፡ የቅድስና እንዲሁም ኢየሱስን በሕይወት ዘመን ሁሉ የማየት ትልቁ ምስጢር መጽሐፍ ቅዱስን በፀሎት ማንበብ ነው፡፡

# ስለ ድነታችን እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን?

ድነትን ማረጋገጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል (ሮሜ 8÷16)፡፡ ለድነት ማረጋገጫን ለማግኘት በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው በቀጥታ ኢየሱስን በመመልከትና ወደ እርሱ በመምጣት ነው፡፡

ድነትን ማረጋገጥ ማተፅን የተባሉ ሰው እንዲህ ብለዋል፤ እግዚአብሔርን በቃሉ መሠረት ለመያዝ ችያለሁኝ፡፡ በመቤዠት ውስጥ ካሉት በረከቶች ሁሉ ጋር ኢየሱስን ብቻ እንጂ ሌላ ማንንም አልመለከትም ነበር፡፡ ሸክሜ ከጀርባዬ ተንከባልሎ ወደቀ፣ ዳንኩኝ፡፡ ደስታዬን ለመቆጣጠር ተሳነኝ፡፡ ድነት በበጉ ደም የሚለውን አዲስ ዝማሬ መዘመር ጀመርኩኝ፡፡ ምሕረትን ያገኘ ኀጢአተኛ የሚሰማው ሰላም በውስጤ ተሰማኝ፡፡ የኢየሱስን ማንነት ብቻ አየሁኝ፡፡ ኢየሱስን በመስቀል ላይ እንዲቸነከር ስላደረገው ኀጢአቴ አለቀስኩ፣ እንባዬም እውነተኛና ከንስሓ የመነጨ እንባ ነበር፡፡

ለዛላለም የእርሱ ብቻ የእርሱ፤

ጌታንና እኔን የሚለየን ማነው እርሱ?

አቤት፤ እንዴት ባለ የእረፍት በረከት
ክርስቶስ አፍቃሪዋን ልቤን ሞላት!

# መንግሥተ ሰማያት - መኖሪያችን

## በወንጌላዊ ደብልዮ ፒ.ኒኮልሰን

ኢየሱስ፣ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው አለ (ዮሐንስ 14÷2)፡፡ የሰውን ልብ የሚያሞቅና ሕልምን እውን የሚደርግ ታላቅ ርእስ ቢኖር መንግሥተ ሰማያት ነው፡፡ በሕይወት ጦርነትና ትግል ደክመን ይሆንን? በቅርቡ እንደገና በማንደክምበት እንዲሁም ሌላ የሕይወት ጦርነትና ትግል በማይኖርበት በመንግሥተ ሰማያት እንደምንሆን ማወቃችን ታላቅ አስደሳች ነገር አይደለምን?

መንግሥተ ሰማያት የብርሃን ቦታ ነች፡፡ በዚያ ጨለማ የሚባል ነገር አይኖርም፡፡ ለዘላለም በቀን፣ በብርሃን እንኖራለን፡፡ ጌታ የመንግሥተ ሰማያት ብርሃንዋ ነው፡፡ ያቺ ብሩህ አገር አንድም ጊዜ በሐዘን ደብዝዛ አታውቅም፡፡ እዚያ ያሉ ሰዎች በሙሉ ነጭ ልብስ ለብሰዋል፡፡ እዚያ በሽታ አይታወቅም፣ እዚህ ግን ከበሽታ የሚያመልጥ የለም፡፡ ከአካላዊ ቁስል ይልቅ ብዙዎች የልብ ቁስል አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ልጇ በኀጢአት ጎዳና እየነጎደ መሆኑን ያየች እናት ታግሳ የቻለችውን ስቃይ ማንም ሊለካው አይችልም፡፡

መንግሥተ ሰማያት በከፍተኛ ብርሃን የተሞላች ስፍራ ስለሆነች የማንም ሰው ዐይን በእንባ አይደበዝዝም፡፡ በዚያ መርገም የለም፡፡ እዚህ ብዙዎች በኀጢአት ምክንያት ተረግመዋል፡፡ የምንሄድባት አገር የኀጢአት መርገምና ጥፋት የተወገዱባት አገር ስለሆነች እግዚአብሔር ይመስገን! መንግሥተ ሰማያት የደስታ ቦታናት፡፡ መላእክቱና የዳኑት ለወደደንና ከኀጢአታችንም በጸሙ ነጻ ላወጣን ... ለእርሱ ክብርና ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን! አሜን (ራእይ 1÷5-6) በማለት እንደሚዘምሩ በቃሉ ውስጥ እንመለከታለን፡፡

# ልጆች በመንግሥተ ሰማያት

የኤደንበርጉ ዶ/ር ጉትሪ ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፣ መንግሥተ ሰማያት የልጆች ስብስብ ናት፡፡ መንግሥተ ሰማይ እነደ እነርሱ ላሉት ናትና (ማቴዎስ 19÷14)፡፡ በሰው እቅፍ ላይ

ሆኖ ለሚሞት ሕፃን ልጅ ይህ እንዴት የሚያጽናና ቃል ነው:: የሕፃናት ሕይወት ገና በጨቅላነቱ ሲቀጭ፣ ጣፋጭና ተወዳጅ የሆነው ሕፃን ልጃችን ነፍስ ሳትጨነቅ ጻጥ ባለ ስቅታ ከውስጡ ወጥታ ወደ መንግሥተ ሰማይ ደስታ አርጋ በመግባት በአምላኳ እቅፍ ላይ ስታርፍ በሞታቸው ሳቢያ በሚደማው ልባችን ላይ እነኚህ የተባረኩ ቃላት እነደሚፈዉስ መድኀኒት ይንጠባጠባሉ::

መንግሥተ ሰማያት ሙሉ የሆነ እውቀት የሚገለጥበት ሥፍራ ነው:: እዚህ እርስ በርሳችን የምንተዋወቀው ፍጹም ባልሆነ መንገድ ነው:: ጭጋጉ ሲገፈፍ ግን በደንብ እነተዋወቃለን:: ጴጥሮስ ከፍ ባለው ተራራ ላይ ሙሴንና ኤልያስን ለይቶ አወቃቸው (ማቴዎስ 17÷1-4):: ንግሥት ቪክቶሪያ በመሞቻዋ ሰዓት ላይ አልበርት! አልበርት! በማለት ከዓመታት በፊት የሞተውን ባልዋን ስትጠራ ተሰምታለች:: አንዲት ሴት ትንሽ ልጇ በምትሞትበት ጊዜ አባዬ! አባዬ! በማለት ከጥቂት ወራት በፊት የሞተውን አባቷን ትጠራ እንደነበር ነግራኛለች::

# አዲሲቱ ኢየሩሳሌም - ሰማያዊ ከተማ

ምን ዓይነት ድንቅ ከተማ ነው የምትሆነው! በዚያ የፈራረሰ ቤት ወይም ሕንጻ ቤት የሚባል ነገር አይኖርም:: ሆስፒታሎች ወይም የእስር ቤቶች በዚያ አይገኙም:: ድኾች ወይም የተጨቌኑ ሰዎች አይኖሩም:: በምድር ላይ ያሉ ታላላቅ ከተሞቻችንን ለእርግማን የዳረጉ ነገሮች በመንግሥተ ሰማያት አይኖሩም:: እግዚአብሔር ያዘጋጃት ከተማ፣ የተሠራችበት የከበሩ ድንጋዮችና ነዋሪዎቿ ለዘላለም የማይጠፉ ናቸው:: ኢያስጲድዋ፣ ዕንቈቾቿና ንጹሕ ወርቅዋ /ራእይ 21÷11፡21/ ሳይጠፉ ለዛላለለም የሚኖሩበት ምክንያት ዳግመኛ የማይሞቱ ቅዱሳን መኖሪያዎች ስለተሰሩባቸው ብቻ ነው:: ከመኖሪያዎቹ በአንዳቸውም የሞት ለቅሶ አይሰማም:: ጎዳናዎችዋን የቀብር ሥርዓት አያጨልሟትም:: በዘላለም ተራሮች ላይ የተቀደሱ ሰዎች ሬሳዎች ያረፉባቸው የሚያብረቀርቁ የመቃብር ሐውልቶች አይገኙም::

የሰማያዊትዋ ከተማ መንገዶች ከንጹሕ ወርቅ የተገነቡ ናቸው:: መኖሪያ ቤቶቹ ትላልቅ ሲሆኑ ነዋሪዎችዋም ቅዱሳንና ደስተኞች ናቸው:: አዲሲቷ ከተማ በሰው እጅ ስላልተገነባች ዘመናት ቢፈራረቁ እንኳ አታረጅም፤ የከተማይቷ ነዋሪዎች ተቈጥረው የማይዘለቁ ሲሆኑ፣ በጎዳናዎቻቸውም ምንም ዓይነት ንግድ አይካሄድም:: ሐዘን ወይም መቃብር፣ ኀጢአት ወይም

ጭንቀት የማይታይበት፣ መሞትና መውለድ የማይሰማበት የጋብቻ ወይም የቀብር የማይካሄድባት ከተማ ነች። ኢየሱስ ንጉሥዋ ከመሆኑ የተነሣ ጠባቂዎችዋ ቅዱሳን መላእክት፣ ዜጎችዋ ቅዱሳን፣ ቅጥርዋ ድነት፣ በሮችዋ ምስጋና ስለሆኑ የከበረች ከተማ ናት።

# የእግዚአብሔር ወህኒ ቤት

## በደብልዩ. ፒ. ኒኮልሰን

በዚህ በሰለጠነው ምድራችን በርካታ እስር ቤቶች አሉን። የሰዎችን ነጻነትና መብት በመግፈፍ በእንደዚህ ዓይነቱ የስቃይ ቦታ ማኖር፣ ከቤታቸውና ከቤተሰባቸው በመለየት ማሳቀቅ እንዲሁም በወዳጆቻቸው ላይ የለቁስልን መሸማቀቅን ማምጣት እንዴት አሳፋሪ ነው። ብዙውን ጊዜ በርካታዎች በወህኒ ቤት የሚታሰሩትና ጥቂቶቹም በስቅላት የሚቀጡት አንድ ወንጀል ስለሰሩ ነው።

በምድራችን ታላላቅ በርካታ የግዞት ቦታዎች አሉን። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ያለፈቃዳቸው በነዚያ ቦታዎች በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ። እንደዚህ ዓይነት ቦታዎች መኖራቸውና ሰዎችን በዚህ መልኩ መያዙ አሳፋሪ ነው። መቼም እንደዚህ በመናገሬ ከየት ነው ይህ ሰው የመጣው? ብለህ እንደማታስብና በሐዘኔታና በፀፀት እንደማትመለከተኝ ተስፋ አደርጋለሁ። እነኚህ ሰዎች ሕግ ተላላፊዎችና እብዶች መሆናቸውን አታውቅምን? በወህኒ ቤት ያኖርዋቸው ታርመው ለራሳቸው መልካም እንዲሆንላቸውና፣ ሀገሪቱና ሕዝቧ ሰላም እንዲኖራቸው ነው ትለኝ ይሆናል።

ለመሆኑ ከእግዚአብሔር የተሻለ አስተዋይነት አለን ብለህ ታስባለህ? ወደ ገሃነም የሚሄዱት ሰዎች እነማን ናቸው? በእግዚአብሔር ላይ ያመፁና በልጁ ደም ከኀጢአታቸው ነጽተው ለመዳን እምቢ ያሉ ወንዶችና ሴቶች ናቸው። በወህኒ ቤት ከማኖር በስተቀር እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የሚያደርገው ሌላ ምን ነገር ይሆናል? ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝ አድርጎ ለመቀበል በፈቃዱ እምቢ የሚል በእርግጥም የገዛ ነፍሱን በሲኦል እንድትኖር የፈረደባት እብድ ሰው ነው። ወንድሞቼና እህቶቼ፣ ሲኦል የእግዚአብሔር ወህኒ ቤት ነው፣ ሲኦል እግዚአብሔር እብዶችን የሚያኑርበት ቤት ነው። በእግዚአብሔር ላይ ማመጽን ብትቀጥልበት እርሱ ለአንተ እስር ቤት አለው፣ ያዘጋጀልህን

ድነት ለመቀበል እምቢ በማለት ሞኝ ብትሆን፣ እግዚአብሔር ላንተ ያዘጋጀው የግዞት ቦታ አለው።

የዚህን ቦታ ባሕርይ ለመግለጽ እግዚአብሔር የተጠቀማቸውን ስያሜዎች እስቲ እንመልከት የእሳት ባሕር፣ ማለቂያ የሌለው ጥልቅ፣ የሚባላ እሳት፣ የሰቆቃ ቦታ፣ የዋይታ ቦታ፣ የልቅሶ ቦታ፣ እቶን እሳት፣ የስቃይ ቦታ፣ የዘላለም እሳት፣ አስጸያፊ ቦታ፣ እግዚአብሔርን የሚሳደቡበት ቦታ፣ የዘላለም ጥፋት፣ የድቅድቅ ጨለማ ስፍራ፣ እረፍት የሌለበት፣ ዘላለማዊ ቅጣት ያለበት፣ ጥርስ ማፋጨት ያለበት ቦታ፣ ለሰይጣንና ለመላእክቱ የተዘጋጀ ስፍራ፣ ጠብታ ውሃ ለማግኘት የሚጮኽበት፣ በእሳትና በዲን የሚሰቃይበት፣ ገሃነመ እሳት፣ ገሃነም፣ የሚመጣው ቁጣ።

እግዚአብሔር ፍቅር ባይሆን ኖሮ ወደ ገሃነም የሚወስደውን መንገድ ቀላልና ፈጣን ባደርገው ነበር፣ ነገር ግን መንገዱን በእሾክና በአሜኮላ ስላጠረው አንድ ሰው ወደ ገሃነም ለመውረድ አብዝቶ ኀጢአት መሥራት ይኖርበታል። ሰው ራሱን ለዘላለም በኩነኔ ውስጥ ከማስቀመጡ በፊት የሚከተሉት ነገሮች አስቀድሞ በሕይወቱ ይፈጸማሉ፤ ደግሞ ደጋግሞ ኅሊናውን በማፈን የእግዚአብሔርን ጥሪ አይሰማም፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ ጸሎትና እንባ ላይ በድፍረት ይረማመዳል፤ የእግዚአብሔርን ቃል አይሰማም፤ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናል፤ ክቡር የሆነውን የክርስቶስን ደም በመርገጥ ያክፋፋል፤ ከዚህ በኋላ ሕይወቱ ለዘላለም ሞት የተጻረገች ትሆናለች።

# ክርስቲያን ለመሆን ምን ማድረግ ይገባል?

## በዶ/.ር አር. ኤ. ቶሬይ

የክርስትና ሕይወትን ለመኖር የማጀምሩ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ፤ እነርሱም ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በመውደቅ የማይሳካላቸው እና ሙሉ በሙሉ በመጽናጽ የሚሳካላቸው ናቸው። ለመሆኑ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ሁሉ ቢጓዝበት ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ግልጽ የሆነ አንድ መንገድ ማሳየት ይቻላልን? የሚለው ጥያቄ ወዲያው ወደ በአእምሮህ ይመጣል። ለዚህ የሚከተለው መልስ አለኝ፣ አዎን፣ አለ ብዬ አምናለሁ። ቢታዘዙት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ስኬትን እርግጠኛ የሚያደርጉ ቀላል የሆኑ ጥቂት መመሪያዎችን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚሰጠን አምናለሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጉዞአችን

ላይ የሚረዱን በሰባት ደረጃ የተቀመጡ የሚከተሉት ምልክቶች አሉ፡-

1. **በትክክል ጀምር፡፡** በዮሐንስ 1፥12 ላይ አስደናቂ የሆነ ትክክለኛ ጅማሬን እናገኛለን፣ ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው፡፡ ክርስቶስን ተቀበል፡፡ ለኀጢአትህ የሞተ አዳኝህ አድርገህ እመነው፡፡ ምሕረት ልታገኝበት የሚገባህን ጉዳይ ሁሉ ለእርሱ ተውለት፡፡ ለኀጢአትህ ሙሉ ቅጣት የሆነን ዋጋ በመክፈሉ በዚህ እውነት ላይ ተደላድለህ ተቀመጥ፡፡

እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው (2ቆሮንቶስ 5፥21)፡፡ በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል (ገላትያ 3፥13)፡፡

ብዙዎች ስህተት የሚሰሩት በዚህ በመጀመሪያው ደረጃ ላይ ነው፡፡ ለድነታቸው መሠረት እንዲሆንባቸው መልካም ሥራቸውን ከዚህ ጋር ለመደባለቅ ይሞክራሉ፡፡ መልካም ከሆኑ፣ በክርስቶስ ሞትና በእነርሱ መልካምነት ምክንያት እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላቸው ያስባሉ፡፡

ኢየሱስን ከኀጢአት ኃይል የሚያድንህ፤ በመተላለፍህና በኀጢአትህ ምክንያት ስትሞት ሕይወት የሚሰጥህ ነጻ አውጪህ፤ ተቤዢህ አድርገህ ተቀበለው፡፡ ራስህን ከኀጢአት ኃይል ለማዳን አትሞክር፡፡ ያንን እንዲያደርግልህ እርሱን እመነው፡፡

ኢየሱስን ጌታህ አድርገህ ተቀበለው፡፡ የገዛ ሕይወትህን ለመምራት አትፈልግ፡፡ በአንተ ላይ ላለው ጌትነት ያለ ምንም መቆጠብ ሙሉ ለሙሉ ራስህን አሳልፈህ በመስጠት ተገዛለት፡፡ ሁሉም ነገር ለኢየሱስ ማለትን ተማር፡፡ ሙሉ በሙሉ ራስን በመስጠት ስለሚያፈነግጡ ብዙዎች ይወድቃሉ፡፡ ኢየሱስን በግማሽ ልባቸው፣ በከፊል ማንነታቸውና ውስን በሆነው ንብረታቸው ብቻ ለማገልገል ይሻሉ፣ ይህ በተከፋፈለ ልብ የሚደረግ የመሰጠት ሕይወት ውጤቱ የማሰናከያ፣ የሽንፈት፣ የሚያሳዝን ኑሮ መሆን ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ የመሰጠት ሕይወት ግን በመንገዳችን ሁሉ ሙሉ ደስታን ያመጣል፡፡

ከዚህ በፊት አልሞከርከው ከሆነና በክርስትና ሕይወትህ ስኬታማ ለመሆን ምኞቱ ካለህ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻህ

ሁንና በጉልበቶችህ ተንበርክከህ ሁሉም ነገር ለኢየሱስ ብለህ በጸሎት አስረክባቸው:: ይህን ጸሎት በቅንነት፣ ከልብህ ጸልይ:: የምታደርገው ነገር ምን እንደሆነ እስከምታውቀውና ትርጉሙ እስከሚገባህ ድረስ በጉልበትህ ቆይ:: አምኖ ለሚራመድ ሰው አስደናቂ የሆነና ወደፊት ሊወሰድ የሚገባ ራስን የመስጠት እርምጃ ነው::

ከዚህ በፊት ይህን እርምጃ ወስደኸውም እንኳን ቢሆን፣ ዛሬም ድገመው:: ደጋግመህ ተራመደው:: ሁል ጊዜ ለሕይወትህ አዲስ ትርጉም አለው፣ ልዩ የሆነ በረከትንም ወደ ሕይወትህ ያመጣል::

ኢየሱስን ጌታህ አድርገህ መቀበል ማለት ጥቃቅን በሆነው የሕይወትህ ክፍል በምታውቀው ጉዳይ ላይ ሁሉ ለፈቃዱ መታዘዝ ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ይኼ አንዱ አይነተኛ መስፈርት ነው፣ እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ (የሐዋርያት ሥራ 5÷32)::

2. በአደባባይ በሰዎች ፊት ስለ ክርስቶስ መስክር:: በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ እኤም በሰማይ ባለው ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ (ማቴዎስ 10÷32):: የምትጸድቀው በልብህ አምነህ ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክረህ ነውና (ሮሜ 10÷10):: በአንደበት የመመስከር ሕይወት የሙሉ ድነት ሕይወት ነው:: ኢየሱስ ስለ እኛ በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክራለሁ ያለው እኛ በሰዎች ፊት ስለ እርሱ ስንመሰክር ነው፤ ይህ ደግሞ የበረከቱን ሙላት ወደ ሕይወታችን ያመጣል::

ስለ ክርስቶስ መመስከር ያለብን አንድ ጊዜ ለምሳሌ ጌታን ስንቀበል ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ያለማቋረጥ፣ በየጊዜው ነው:: በክርስትና ሕይወቱ የላቀ ስኬት የሚያገኝ ክርስቲያን በቤቱ፣ በገበያ፣ በሥራው ቦታ፣ በቤተ ክርስቲያንና በስፍራ ሁሉ የሚያገኘውን አጋጣሚና እድል ስለ ክርስቶስ በሰዎች ፊት የምስክርነት ሕይወትን የሚጠቀምበት ሰው ነው::

አንድ ጊዜ በእድሜና በእውቀት የበሰሉ አንድ ሰባኪ፡-ክርስቶስን ብናከብረው እርሱ እኛን ያከብረናል ብለው ሲናገሩ ሰምቻለሁ:: እዚህ ላይ ሲደርሱ ስንቶች ክርስቶስን ካዱት! አገር ሲለውጡ ወይም ወደ አዲስ የሥራ ቦታ ሊዛወሩ ስለ ክርስቶስ መመስከርን ቸል በማለት ወደ ዓለም የሚመለሱ ስንቶች ናቸው?

3. ቃሉን አጥና፡፡ በድነታችሁ እንድታድጉ፣ አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ፤ (ጴጥሮስ 2÷2)፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የነፍስ ምግብ ነው፡፡ ቃሉ የአዲሱ ሕይወት ማፋፊያ ንጥረ ነገር ነው፡፡ ቃሉን ችላ የሚል ሰው በክርስትና ሕይወቱ ስኬታማ አይደለም፡፡ በክርስትና ሕይወት ጉዞ ዘላቂ የሚሆኑ ቃሉን በከፍተኛ ደረጃ የሚመገቡ ናቸው፡፡ ብዙዎች እዚህ ላይ ተሸንፈው ይወድቃሉ፡፡ ጌታን ትቶ ወደ ዓለም የገባውን ሰው በየቀኑ ቃሉን ታነብብ ነበር? ብለህ ጠይቀው፡፡ አዎን ብሎ የሚመልስ አንድም ሰው እስከ አሁን አላገኘሁም፡፡

መጽሐፈ ቅዱስን ስለ ማንበብ ሁለቱ ዋና ዋና ነጥቦችን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፤ በመጀመሪያ ለራስህ ለነፍስህ ምግብ እንዲሆንልህ አንብብ፤ ሁለተኛ በጉልበትህ ተንበርክከህ ሰፊ ጊዜ ወስደህ ብዙ ምዕራፍ አንብብ፡፡ በጉልበቴ ተንበርክኬ ማንበብ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በተወሰነ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኔ አዲስ መጽሐፍ ሆኖልኛል፡፡

4. ሳታቋርጥ ጸልይ፤ (1 ተሰሎንቄ 5÷17)፡፡ በክርስትና ስኬታማ ሕይወት እንዲኖረው የሚፈልግ ሰው የጸሎት ሕይወት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይኼ ካሰብክበትና ካቀድከው ብቻ ቀላል ይሆናል፡፡ ዳዊትና ዳንኤል በቀን ውስጥ ሦስት ጊዜ ለመጸለይ መወሰናቸው በእርግጥም መልካም ውሳኔ ነበር፡፡

በማታ፣ በጥዋትና በቀን፣ እጮኸለሁ፤ እቃትታለሁ፤ እርሱም ድምጼን ይሰማኛል መዝሙር 55÷17፡፡ ዳንኤልም ዐዋጁ እንደ ወጣ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ሄደ፤ መስኮቶቹ በኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው ባሉበት በሰገነቱ ቀድሞ ያደርግ እንደ ነበረው በቀን ሦስት ጊዜ ተንበርክኮ ጸለየ፤ አምላኩንም አመሰገነ (ዳንኤል 6÷10)፡፡

ቀኑን በጸሎትና በምስጋና ጀምር፤ ባለፈው ላገኘኸው ምሕረት ምስጋናን አቅርብ፣ ለዛሬው ቀን ደግሞ ለሚያስፈልግህ ጉዳይና ሁሉ ልመናህን አቅርብ፡፡ በቀኑ ፈተና፣ ጭንቀትና ሁካታ መካከል ቆም ብለህ ለማመስገንና ለመጸለይ ጊዜ ውሰድ፡፡ ቀኑ ሲመሽ በምስጋና ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ቀርበህ በሰላም እረፍ፡፡

የተለየ ፈተና ወደ ሕይወትህ ሲመጣና ሲቀርብህ ጸሎት ያስፈልግሃል፡፡ ያለማቋረጥ በመጸለይ የተለየ እግዚአብሔርን የመመልከት ሕይወት ይኑርህ ሕይወትህ እንዲህ ከሆነ ስትጸልይ

ሁልጊዜ መንበርከክ ላይስፈልግህ ይችላል። ይሁን እንጂ ልብህ ሁልጊዜ መንበርከክ ይኖርበታል። ደካማ ክርስቲያን ተንበርክኮ ሲጸልይ ሲያይ ሰይጣን የሚንቀጠቀጥ ከሆነ ሳያቋርጥ እንዲንቀጠቀጥ እናድርገው። በጉልበታችን ተንበርክከን መጸለይን የዘውትር ባሕርያችን እናድርገው። ይህም ከጭንቀትና ከስጋት ነጻ የሆነ ደስተኛ ሕይወት እንዲኖረን ያደርጋል፤ ብዙዎች ግን ጸሎትን ችላ በማለታቸው ይወድቃሉ።

በክርስትና ሕይወቱ ስኬታማ የሚሆን ሰው ሊጸልይባቸው የሚገቡ የሚከተሉት ሦስት ነገሮች ናቸው። አንደኛ እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠው፤ ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል (ያዕቆብ 1÷5)። ሁለተኛ እግዚአብሔር ኃይልና ብርታት እንዲሰጠው፤ እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን ኀይላቸውን ያድሳሉ (ኢሳይያስ 40÷31)። ሦስተኛ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ፤ የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ! (ሉቃስ 11÷13)። በእያንዳንዱ የአገልግሎትህ የችግርና የመከራ ጊዜ በአዲስ መልክ በመንፈስ ቅዱስ እንድትሞላ ጸልይ (ሐዋርያት ሥራ 4÷31)።

5. **የክርስቶስን *ሥራ* ለመ*ሥራ*ት ተነሣ፤** ላለው ይጨመርለታል፤ የተትረፈረፈም ይኖረዋል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወስድበታል (ማቴዎስ 25÷29)። የዚህን ጥቅስ ዐውድ ምንባብ ስትመረምር፣ ያላቸውን ስጦታ የሚጠቀሙበት ሌላ ተጨማሪ እንደሚያገኙ፣ ያላቸውን ስጦታ ቀብረው የሚያስቀምጡና የማይጠቀሙበት ደግሞ ያንን ያላቸውን እንኳን እንደሚያጡት ይናገራል።

በ*ሥራ* የተጠመደ አማኝ ጥቂትም ሆነ ብዙ፤ ያለውን ተሰጥኦ ለክርስቲያናዊ አገልግሎት የሚያውል ያ ሰው በምድር የክርስትናን ሕይወት በሚገባ ይኖራል፤ በመንግስተ ሰማይም፣ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ (ማቴ 25÷23) የሚለውን አስደናቂ የጌታውን ድምጽ ይሰማል።

ለክርስቶስ ልትሠራ የምትችለውን ሁሉ አድርግ፤ መልካም *ሥራን* ለመ*ሥራ*ት ተመኝ። ሌሎች ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ መጋበዝ ወይም መንፈሳዊ የሆነ በራሪ ወረቀት ማደል እንኳን ቢሆን ሳትንቅ አገልግል። ሁልጊዜ ለክርስቶስ የሚሆነውን *ሥራ* ፈልገህ *ሥ*ትሰራ፤ ከክርስቶስ የምትቀበለው ብዙ ነገር ይኖርሃል።

6. **በልግስና ስጥ፡፡** ለጋስ ይበለጽጋል፤ ሌሎችን የሚያረካም ራሱ ይረካል፡፡ (ምሳሌ 11÷25)፡፡ ይህን አስታውሱ፤ ጥቂት የዘራ ጥቂት ያጭዳል፤ ብዙ የዘራ ብዙ ያጭዳል፡፡ ሁል ጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ እንድትትረፈረፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል (2ቆሮንቶስ 9÷6፡8)፡፡

በክርስትና ሕይወት ማደግና ስኬት በልግስና ከመስጠት ሕይወት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስግብግብ ክርስቲያን እድገት አይታይበትም፡፡ ክርስቲያን መስጠት ሲጀምር ማደግ መጀመሩ በጣም አስደናቂ ጉዳይ ነው፡፡ በእቅድና በሥርዐት ስጥ፡፡

ከምታገኘው ገንዘብ ላይ የተወሰነ መጠን በመለየት ለክርስቶስ የምትሰጠውን አዘጋጅ፡፡ የለየኸውን ገንዘብ ለሌላ ጉዳይ ሳታውል በታማኝነት ሳታጎድል ለክርስቶስ ስጥ፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን የለየኸውን ገንዘብ ለግል ጥቅምህ አታውለው፡፡ ከምታገኘው ገንዘብ አንድ ዐሥረኛው ዐሥራት ይባላል፡፡ ያንን ለጌታ በመስጠት ጀምር፡፡ ዐሥራትህ ከአንድ ዐሥረኛው በታች አይሁን (ለምሳሌ 100 ብር ብታገኝ ከዚያ ውስጥ ዐሥሩ ብር የጌታ እንጂ የአንተ አይደለም፡፡) ዐሥራት በመስጠት የሚገኘውን ደስታና በረከት ስትለማመድ ከዐሥራት በተጨማሪ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተውን መባንና የፍቅር ሥጦታን መስጠት በቀጣይነት ትማራለህ፡፡

7. **ወደፊት ሂድ ፤** ወንድሞች ሆይ፤ እኔ እንደ ያዝሁት አድርጌ ራሴን አልቁጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ (ፊልጵስዮስ 3÷13-14)፡፡ ከኋላህ ያለውን ያለፈውን እርሳው፤ ከፊትህ ያሉትን የተሻሉ በረከቶች ለመጨበጥ ግን ወደፊት ግፋ፡፡

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ፡፡ ያሳለፍከውን የኀጢአት ሕይወት እርሳው፡፡ አሁንም እንኳን በኀጢአት ወድቀህ ብትሆን፣ ወደ ፊትም ብትሰናከል፣ ተስፋ አትቁረጥ፣ ጉዞህን አታቁም፣ ስለ ኀጢአትህ አትተክዝ፡፡ ወዲያው ንስሓ ግባ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል እመን፡፡ ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው (1ዮሐንስ 1÷9)፡፡

ኀጢአትህ ይቅር እንደተባለ እመን፤ ወደ ፊት ተጓዝ። ሰይጣን ብዙዎችን ምስኪን ነፍሳት የሚያታልለው እዚህ ነጥብ ላይ ነው። በኀጢአታችንና በውድቀታችን ላይ እንድንተክዝ ያደርገናል። እግዚአብሔር ኀጢአታችሁን ደምስሼዋለሁ፣ ረስቼዋለሁ ብሎ የተናገረውን ቃል በመጠራጠራችንና ባለማመናችን ምክንያት እርሱን ውሸታም ማድረጋችንን ትህትና እንደሆነ አድርገን እንድናስብ ያደርገናል።

ያለፈውን ስኬትና ድል እርሳውና የተሻለውን ለመያዝ ወደፊፍ ተጓዝ። ይህ እንዳይሆን፣ ሰይጣን ብዙዎቻችንን ያታልለናል። ያገኘነውን መልካም ነገር ብቻ እንድናሰላስልና በዚያ እንድንረካ፣ ብሎም በትዕቢት እንድንነፋ በማድረግ ቢቻለው ወደ ዓለም እንድንመለስ ካልሆነም ባለንበት እንድንቆም ያደርገናል። ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክምንደርስ (ኤፌሶን 4÷13)፤ ሁልጊዜ ዛሬ ከያዝነው ነገር የተሻለና የበለጠ ከፊታችን አለ።

# አዳኙ እና ኀጢአተኛው ኀጢአተኛው

የኀጢአት ደምዎዝ ሞት ነው። (ሮሜ 6÷23)።

እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ (ሉቃስ 18÷13)።

እድን ዘንድ ምን ላድርግ? (ሐዋርያት ሥራ 16÷30)።

# አዳኙ

የእግዚአብሔር ስጦታ በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው (ሮሜ 6÷23)። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፤ (ዮሐንስ 3÷16)።

# ኀጢአተኛው

ራሴን እንቃለሁ፤ በትቢያና በዐመድ ላይ ተቀምጬ ንስሓ እንገባለሁ (ኢዮብ 42÷6)። ፊትህን ከኀጢአቴ መልስ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ (መዝሙር 51÷9)።

# አዳኙ

መተላለፊ እንደ ደመና፣ ኀጢአትህን እንደ ማለዳ ጭጋግ ጠርጌ አስወግጃለሁ፤ ተቤዥቼሃለሁና ወደ እኔ ተመለስ (ኢሳያስ 44÷22)፡፡

# ኀጢአተኛው

ከፊትህ አትጣለኝ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድ (መዝሙር 51÷11)፡፡

# አዳኙ

ከእናንተ መካከል አንዱ መቶ በጎች ቢኖሩትና ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋበት፣ ዘጠና ዘጠኙን በሜዳ ላይ ጥሎ የጠፋውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ተሸክሞ፣ ወደ ቤቱ ይመላለሳል፤ (ሉቃስ 14÷4-6)፡፡

የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው፡፡ (ሉቃስ 19÷10)፡፡

# ኀጢአተኛው

እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን አስተምረኝ፤ (መዝሙር 27÷9)፡፡

# አዳኙ

መጻሕፍትን መርምር (ዮሐንስ 5÷39)፡፡

ቅዱሳን መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ (2ጢሞቴዎስ 3÷16)፡፡

# ኀጢአተኛው

ከሕግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ፣ ዐይኖቼን ክፈት (መዝሙር 119÷18)፡፡

አዳኝ አምላኬ ሆይ፤ አትጣለኝ፤ አትተወኝም፡፡ (መዝሙር 27÷9)፡፡

# አዳኙ

ከቶ አልተውህም፤ በፍጹም አልጥልህም፡፡ (ዕብራውያን 13÷5)፡፡

በዘላለማዊ ፍቅር ወድጄሻለሁ፤ ስለዚህም በርኅራኄ ሳብሁሽ:: (ኤርምያስ 31÷3)::

ትወዳኛለህን? (ዮሐንስ 21÷17)::

## ኀጢአተኛው

ጌታ ሆይ፤ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንደምወድህም ታውቃለህ:: (ዮሐንስ 21÷17)::

## አዳኙ

ብትወደኝ ትእዛዜን ጠብቅ (ዮሐንስ 14÷15)::

አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ (ዮሐ 13÷34)::

## ኀጢአተኛው

በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ፤ ነገር ግን ልፈጽመው አልቻልሁም:: የማደርገው ሳደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም፤ ዳሩ ግን ለማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር ነው (ሮሜ 7÷18-19)::

## አዳኙ

ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና:: (2ቆሮንቶስ 12÷9)::

## ኀጢአተኛው

ጌታ ሆይ፤ እምነታችንን ጨምርልን (ሉቃስ 17÷5)::

## አዳኙ

ለምኑ ይሰጣችኋል፤ (ሉቃስ 11÷9)::

አባት ሆኖ ሳለ ልጁ ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው ይኖራልን? (ሉቃስ 11÷11)::

እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት፣ የሰማይ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ! (ሉቃስ 11÷13)::

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው (ገላትያ 5÷22-23)።

ማስታወሻ፡- ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

(መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ታተመ 1993 ዓ.ም.)።

For further copies of this booklet please write to –

Revival Movement Association,

2 Clara Street,

Belfast,

BT5 5GB,

N. Ireland.